የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

FDRE CIVIL SERVICE COMMISSION

# የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች በስራ ላይ ለሚደርስ ጉዳት የህክምና ወጪ አከፋፈል መመሪያ

ታህሳስ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች በስራ ላይ ሳሉ ለሚደርስ ጉዳት የህክምና ወጪ አከፋፈል መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. "አዋጅ›› ማለት የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ነው፡፡
2. "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመና ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር የፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፤
3. "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፡፡
4. "ጊዜያዊ ሠራተኛ" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የዘላቂነት ባሕርይ በሌለው ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው፤
5. "የሥራ ሁኔታ" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በመንግሥት ሠራተኞች መካከል ያለ ጠቅላላ የሥራ ግንኙነት ሲሆን ይህም የሥራ ሰዓትን፣ ደመወዝን፣ ልዩ ልዩ ፈቃዶችን፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነትን፣ የሠራተኞች የሥራ ስንብት ሁኔታና ክፍያ፣ የዲሲፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓቶችን እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡
6. "የህክምና ወጪ" ማለት አንድ የመንግስት ሰራተኛ ከስራ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚደርስበት ጉዳት ለሀገር ውስጥ ህክምና የሚከፈል ገንዘብ ነው፡፡
7. ‹‹በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት›› ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission
Samuel Gima Legal Consultant & Attorney

8. ‹‹በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ›› ማለት የመንግስት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡
9. ‹‹በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ›› ማለት የመንግሥት ሠራተኛው ከሚሠራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሳ በሽታን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ወይም በሽታዎችን በማጥፋት ስራ ተሰማርቶ እያለ ባለበት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን፣ ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና ስር የሰደዱ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም፡፡
10. ‹‹የአካል ጉዳት›› ማለት የመሥራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡
11. ‹‹ጊዜያዊ የአካል ጉዳት›› ማለት ለተወሰነ ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል የመሥራት ችሎታን ማጣት ነው፡፡
12. ‹‹ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት›› ማለት የመሥራት ችሎታ የሚቀንስ የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡
13. ‹‹ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት›› ማለት ጉዳት የደረሰበትን የመንግሥት ሠራተኛ ማናቸውንም ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡
14. ‹‹የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች›› ማለት በስራ ቦታ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን ለመከላከል የሚሰጥ መሳሪያ ነው፡፡
15. “የህክምና ተቋም” ማለት በሀገር ውስጥ አግባብ ባለው ባለስልጣን ፍቃድ የተሰጠው የመንግስት ወይም የግል የህክምና ተቋም ነው፡፡

3. የጾታ አገላለጽ፤

በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ላይ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን

በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 2 የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት ሰራተኛ እና ጊዜያዊ ሰራተኛ በሚል ትርጉም በሚሸፈኑ ሰራተኞችና መስሪያ ቤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

5. **የመመሪያው ዓላማ**

በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሥራ ላይ አደጋ ስጋቶችን፣ በሥራ ምክንያት በሰራተኛው ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በመከላከል እና ጉዳት ሲደርስም ተገቢውን ህክምና እንዲያገኝ ወጪውን በመሸፍን የስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነትን መፍጠር ነው።

## ክፍል ሁለት

### 6. በስራ ላይ ለሚደርሱ አደጋዎች የህክምና ወጪ አከፋፈል

1. በሥራው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የመንግስት ሠራተኛ በሀገር ውስጥ በሚገኝ የመንግስት የሕክምና ተቋም ህክምናውን ተከታትሎ የህክምና ማስረጃ ካቀረበ በአዋጁ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለሚከተሉት የሕክምና አገልግሎቶች የሚያስፈልገው ወጪ በመሥሪያ ቤቱ ይሸፈናል፡፡
    1) የጠቅላላና የልዩ ሕክምና፤
    2) የቀዶ ሕክምና፤
    3) የሆስፒታልና የመድኃኒት፤
    4) የማንኛውም አስፈላጊ ሰው ሰራሽ ምትክ ወይም ተጨማሪ አካሎችና የአጥንት ጥገና ወጪዎች፡፡
2. ጉዳት ለደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ የህክምና አገልግሎት በግል የህክምና ተቋም እንዲሰጠው የሚደረገው በአዋጁ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አገልግሎቱ በመንግሥት የሕክምና ተቋማት ሊሰጠው የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡
3. የመንግስት ሰራተኛ በመስክ ስራ ላይ እያለ ድንገተኛ ጉዳት ሲያጋጥመው በአካባቢው በቅርበት በሚገኝ ህጋዊ እውቅና ባለው ማንኛውም የህክምና ተቋም እንዲታከም በማድረግ ወጪውም በሚቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ ይሸፈናል፡፡
4. የመንግስት ሰራተኛው በስራ ላይ ድንገተኛ ጉዳት ሲያጋጥመው መስሪያ ቤቱ በአካባቢው በቅርበት በሚገኝ ህጋዊ እውቅና ባለው ማንኛውም የህክምና ተቋም በራሱ ማጓጓዝ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን መስሪያ ቤቱ አገልግሎቱን ማቅረብ ካልቻለ ሰራተኛው ለትራንስፖርት ላወጣው ወጪ የሚያቀርበውን ማስረጃ ከሀገሩ የትራንስፖርት ታሪፍ ጋር በማነፃፀር እና በማረጋገጥ ወጪውን ይሸፍናል፡፡ ከተረጋገጠው ታሪፍ በላይ የሚገልፅ መረጃ ቢያቀርብ ተጨማሪውን ወጪ ሰራተኛው እራሱ ይሸፍናል፡፡
5. የመንግስት ሰራተኛው በስራ ላይ እያለ ጉዳት ሲደርስበት ወጪውን በቀጥታ መክፈል የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥም መስሪያ ቤቱ የዱቤ ህክምና እንዲያገኝ ከህክምና ተቋሙ ጋር በመነጋገር እርዳታውን የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
6. የስራ ባህሪያቸው ለኬሚካል፣ ለጨረር፣ ለብናኝና ለከፍተኛ ሽታ በሚያጋልጡ የስራ መደቦች ላይ ተመድበው ለሚሰሩ ሰራተኞች ጤንነታቸውን ለመጠበቅ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ

መሰረት፣ በመንግስት የሕክምና ተቋም ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ የጤና ምርመራ እንዲያገኙ ከአንድ የመንግስት የህክምና ተቋም ጋር ይዋዋላል፡፡

7. የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 53 ንኡስ አንቀፅ (2) (ሐ) በተደነገገው መሰረት የመንግሥት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው መንግስት ለሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም መስሪያ ቤቱ ለዚህ ተግባር በተከራየውና በግልፅ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ በመንግስት ሰራተኛው ላይ ለሚደርስ ጉዳት በዚህ መመሪያ መሰረት የህክምና ወጪው እንዲሸፈን ያደርጋል፡፡

## 8.የህክምና ምርመራና የመድሐኒት ግዢ አፈፃፀም

በስራ ላይ ጉዳት የደረሰበት የመንግስት ሰራተኛ ምርመራና የመድሀኒት ግዢ በሐኪም ሲታዘዝ አገልግሎቱ በመንግስት የህክምና ተቋም አለመኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ከግል የህክምና ተቋምና ፋርማሲዎች ምርመራውን በማድረግ ወይም ግዢ በመፈጸም በሚያቀርበው ደረሰኝ መሰረት ወጪው በመስሪያ ቤቱ እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡

በዙበህ ጉበረያስ በየነ
ኮሚሽነር

## ክፍል ሶስት

### 9. የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ተግባርና ሀላፊነት

1. የመንግስት ሰራተኞች በስራ ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የመከላከያ ዘዴዎችን ተግባራዊ የማድረግ፤
2. ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ ህይወትን ለማትረፍና ዘላቂ ጉዳት እንዳያስከትል የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ የሚሰጥበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤
3. የመንግስት ሰራተኛው በስራ ላይ እያለ ጉዳት ስለመድረሱ እና ተገቢውን ህክምና ማግኘቱን የሚቀርቡ መረጃዎችን በስራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ባለሙያ ወይም በሚመለከተው አካል የማረጋገጥ፣
4. የሕክምና ወጪ የሚሸፈንበትን በጀት ማስመደብ ወይም የጤና መድህን መግባት፣
5. በስራ ቦታ ላይ ለሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች እና ለሚመለከታቸው አካላት በስራ ምክንያት ለደረሰ ጉዳት የሚከፈል የህክምና ወጪን በተመለከተ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲተገበሩ ግንዛቤ የመፍጠር፤
6. ለአካል ጉዳተኞች፣ ለነፍሰጡር ሴቶች እና የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝባቸው ሰራተኞች ከስራ ጋር በተያያዘ ለጉዳት እንዳይዳረጉ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት፣
7. የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ ማቅረብ፣ ስለአጠቃቀሙ ሥልጠና መስጠት እና በትክክል የሚሰሩ መሆኑን የመከታተል፣
8. የመንግስት ሰራተኛውን በተደጋጋሚ ለጉዳት የሚያጋልጥ የስራ ባህርይን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ የመውሰድ፣
9. በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ ተገቢውን ህክምና እንዲያገኝ የማድረግ፤
10. የመንግስት ሰራተኛው በስራ ላይ ጉዳት ደርሶበት በራሱ ወጪ ህክምና ካደረገ ያወጣውን ወጪ እንዲመለስለት ተገቢውን ማስረጃ አሟልቶ፣ ጥያቄው በቀረበ 10 የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ የመክፈል፣
11. በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ በተሰጠው ህክምና ምክንያት ተጨማሪ የጤና መቃወስ ካልደረሰበት በስተቀር በሐኪም የተሰጠውን ትዕዛዝ በአግባቡ አለመፈፀሙ በሐኪሙ ከተረጋገጠ የሚሰጠው ህክምና እና የህመም ፈቃዱ እንዲቋረጥ የማድረግ ፣
12. በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ሰራተኛው ህይወቱ ቢያልፍ የህክምና ወጪውን ለህጋዊ ወራሹ የመክፈል፣ አስክሬኑን ወደ ቤተሰቦቹ ለማድረስ የመስሪያ ቤቱ ተሽከርካሪ

እንዲመደብ የማድረግ ወይም ለዚሁ ጉዳይ የሚያስፈልገውን ወይም የወጣውን ወጪ የመሸፈን እንዲሁም በአዋጁ አንቀፅ 60 ላይ የተደነገጉት መብቶቹ እንዲጠበቁለት የማድረግ፣

ተግባርና ኃላፊነት አለበት፡፡

## 10. የመንግስት ሰራተኛው መብት

ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ፣

1. ለስራው የሚያስፈልገውንና የተፈቀደለትን የአደጋ መከላከያ መሳሪያና ቁሳቁስ የማግኘት፤
2. በስራ ምክንያት ጉዳት ከደረሰበት ህክምና እንዲደረግለት የመጠየቅና የማግኘት፤
3. ለበሽታ የሚያጋልጥ የስራ መደብ ላይ ተመድቦ የሚሰራ ሰራተኛ በአመት ሁለት ጊዜ የጤና ምርመራ የማግኘት፤

መብት አለው፡፡

## 11. የመንግስት ሰራተኛው ግዴታ

ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ፣

1. ለስራው የተሰጠውን የአደጋ መከላከያ መሳሪያና ቁሳቁስ በአግባቡ የመጠቀም፤
2. በስራ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት የወሰደውን የህክምናና የመድሂኒት ወጪ ህጋዊ ማስረጃ የማቅረብ፣
3. የህክምና ማስረጃውን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ህክምናውን እንደጨረሰ የማቅረብ ፣
4. በስራ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት የሐኪም ትዕዛዛትን ተከትሎ ህክምናውን በአግባቡ የመከታተል፤
5. በመደበኛ ስራም ሆነ በመስክ ስራ ላይ እያለ በራሱ ላይም ሆነ በሌሎች ሰራተኞች ላይ ለጉዳት ሊያጋልጥ የሚችል ክስተት መኖሩን ሲመለከት ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ የማሳወቅ፣

ግዴታ አለበት፡፡

ስለብሀ ጉብረየስ በየነ

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. ተጠያቂነት

1. ገንዘብ ለማግኘት በማሰብ አግባብነት የሌለው የህክምና ማስረጃ ማቅረብ ያቀረበውን ሰራተኛ በወንጀል የሚያስጠይቅ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ከሕግ ውጭ ለሚፈጽማቸው ተግባራት ሁሉ በአዋጁ አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. ኮሚሽኑ ይህንን መመሪያ በተገቢው ሁኔታ በማይተገብሩ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፡፡

### 13. የቅሬታ አቀራረብ

ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ቅሬታ ያለው ከሆነ በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች የዲሲፒሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት በደንብ ቁጥር 77/1994 መሰረት ቅሬታውን በማቅረብ ምላሽ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

### 14. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 15. መመሪያውን ስለማሻሻል

ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

### 16. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኮሚሽነር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

በሁበሁ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር